የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 20
ADDIS ABABA, 7th May, 2026

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻/፪ሺ፲፰

የዕፅዋት ጥበቃና ኳራንቲን አዋጅ…....................................................................ገጽ ፲፱ሺ፮፻፫

**Content**

Proclamation No. 1400/2026

Plant Protection and Quarantine Proclamation…............................Page 19603

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻/፪ሺ፲፰

## የዕፅዋት ጥበቃና ኳራንቲን አዋጅ

በሀገራችን ደረጃውን የጠበቀ ተባይ አሰሳ እና ቅኝት በማካሄድ፣መረጃ በማሰባሰብ በመተንተን ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን በመዘርጋት እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የዕፅዋት ተባይ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ እና አካባቢያዊ ጉዳት የሚቀንስ ዘመናዊ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በምርትና ምርታማነት እድገት ላይ አስተዋፅኦ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሀገራችን የተቀበለችውን ዓለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት መሠረት በማድረግ ዕፅዋትን፣ የዕፅዋት ውጤትን እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን ተቆጣጥሮ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ወደ ውጭ ለመላክ፤ በዓለም አቀፍ ገበያ በሚኖረው ዝውውር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳርፍ ለማድረግ፤ ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ከገባም እንዳይስፋፋና እንዳይሰራጭ ህጋዊ መሰረት ያለው ጠንካራና ውጤታማ የሆነ የዕፅዋት ኳራንቲን ሥርዓት መኖር አስፈላጊ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1400/2026

## PLANT PROTECTION AND QUARANTINE PROCLAMATION

**WHEREAS,** it is important to enhance production and productivity by carrying out standard plant pest surveys and surveillance, data collection, and analysis, and establishing an early warning system in collaboration with relevant stakeholders for implementation of modern prevention and control technology to reduce the economic, social, and environmental damage caused by pests;

**WHEREAS,** it is required to establish a strong and effective Plant quarantine legislative system in the country to implement the International Plant Protection Convention to which the country is a contracting party to regulate the import and export of plants, plant products, and other regulated articles, restrict the entry and spread of pests without a serious negative effect on the movement of plants, plant products, and other regulated articles in international trade; and

ዕፅዋትንና አዝርዕትን ለመጠበቅ የወጣው ድንጋጌ ቁጥር ፶፮/፩ሺ፱፻፶፫ ወቅቱን ባገናዘበ ሁኔታ የዕፅዋት ጥበቃና ኳራንቲን ሥራ ለመሥራት የዓለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት ባወጣቸው ደረጃዎች ያልተቃኘ በመሆኑ እና የተቀናጀ የተባይ መከላከል እና ቁጥጥር ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ዘመናዊ ሥርዓት በመዘርጋት ተባይ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ እና አካባቢያዊ ጉዳት መቀነስ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የዕፅዋት ጥበቃና ኳራንቲን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ዕፅዋት"** ማለት ማንኛውም ሕይወት ያለው ተክል ሆኖ የተክሉ አካል የሆነውን ዘርና ብዛ-ዘርንም ያካትታል፤

**WHEREAS,** the Plant Protection Decree No. 56/1963 is not aligned with the standards established by the International Plant Protection Convention to carry out plant protection and quarantine activities in a contemporary manner; and whereas, the existing system does not follow an Integrated Pest Management and control approach; **WHEREAS,** it has become necessary to establish a modern system to mitigate the economic, social, and environmental damage caused by pests;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Plant Protection and Quarantine Proclamation No. 1400/2026".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context of the word or phrase otherwise requires:

1/ **"Plant"** means any living plants and parts thereof, including seeds and germplasm;

፪/ **“የዕፅዋት ውጤት”** ማለት ማንኛውም ከዕፅዋት የሚገኝ በፋብሪካም ሆነ ከፋብሪካ ውጪ የተቀነባበረም ሆነ ያልተቀነባበረ በባህሪው ወይም በማቀነባበር ሂደት ለተባይ መግባትና መስፋፋት ስጋት የተጋለጠ ምርት ነው፤

፫/ **“ዘር”** ማለት ለዕፅዋት ማራባት የሚያገለግል እውን ዘር፣ አኩራች፣ የተክል ቁርጥራጭ፣ ሥራ-ሥር፣ ችግኝ፣ ሳየን፣ መሰረተ ግንድ ወይም ሌላ ዓይነት የተክል አካል ሆኖ ለፍጆታ ወይም ለማቀነባበሪያ እንዲውል ያልታሰበ ነው፤

፬/ **“አትክልትና ፍራፍሬ”** ማለት ለምግብነት ወይም ለማቀነባበር ሊውል የታሰበ ሊበቅል ወይም ሊራባ የሚችል ዕፅዋት ሲሆን ለዘርነት ዓላማ እንዲውል ያልታሰበ ነው፤

፭/ **“የቲሹ ካልቸር ዕፅዋት”** ማለት ማንኛውም የዕፅዋት ህዋስ፣ ሕብረ ህዋስ ወይም አካል በመውሰድ ከማንኛውም ዕፅዋትን ሊጎዳ ከሚችል ባዕድ ህይወት ካለው ነገር ነፃ መሆኑን በማረጋገጥ በአመቺ መያዥና ማሳደጊያ በማደግ ላይ ያለ ዕፅዋት ነው፤

፮/ **“ልውጥ-ህያው”** ማለት ሰው ሠራሽ የሆነ ወይም ከሌላ ህያው ወይም ከቅሪት ከተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ስለተካተተበት የዘረመሎች ይዘቱ ወይም ባህሪው ክስተት የተለወጠበት ሕያው ነው፤

2/ **“Plant Product”** means any plant-based product, regardless of whether it has been processed or remains in its natural state, exposed to a risk of introduction and distribution of pests due to its inherent properties or the methods used in its processing;

3/ **“Seed”** means botanical seeds, tuber, cutting, bulb, seedling, scion, and tissue cultured plants or any other material for planting or intended for planting and not for consumption or processing;

4/ **“Fruit and Vegetable”** means intended for consumption or processing but not for propagation although it is a plant part that has the potential of reproducion or propagation;

5/ **“Tissue Cultured Plant”** means any part of a plant or plant tissue or plantlet grown under aseptic or sterile conditions in flasks or other suitable container on appropriate media;

6/ **“Genetically Modified Organism”** means any living organism that has been artificially created or modified by altering the composition or characteristics of its genetic material through the transfer, or reengineering of genetic material from another organism or source, including fossil-derived or newly engineered genetic material;

፯/ **"ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ"** ማለት ማንኛውም የማከማቻ ቦታ፣ ማሸጊያ፣ ማጓጓዣ፣ መያዣ፣ አፈር፣ እና ሌላ ተባይን ሊሸከም ወይም ሊያሰራጭ የሚችል በተለይም በዓለም አቀፍ ማጓጓዣ የሚጓጓዝ እና የዕፅዋት ጤንንት እርምጃ የሚያስፈልገው ቁስ ነው፤

7/ **"Other Regulated Article"** means any storage place, packaging, conveyance, container, soil, and any other organism, object, or material capable of harbouring or spreading pests, deemed to require quarantine measures, particularly where international transportation is involved;

፰/ **"የእንጨት ማሸጊያ"** ማለት ለሸቀጥ መደገፍያ፣ ለመከላከያ ወይም ለመያዣነት ወይም ለመደርሪያነትና መሸከሚያነት የሚያገለግል እንጨት ወይም የእንጨት ውጤት ሲሆን የወረቀት ውጤትን አያካትትም፤

8/ **"Wood Packaging Material"** means wood or wood products used in supporting, protecting, containing or shelving and carrying a commodity includes dunnage but excluding paper products;

፱/ **"ሸቀጥ"** ማለት ለንግድ ወይም ለሌላ ተግባር የሚዘዋወር ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ዓይነት ነው፤

9/ **"Commodity"** means a type of plant, plant product, or other regulated article being moved for trade or other purpose;

፲/ **"ጭነት"** ማለት መጠኑ የታወቀ በአንድ የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተካተተ ዕፅዋት ወይም የዕፅዋት ውጤት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ በተናጠል ወይም በድብልቅ በመዘዋወር ላይ ያለ ቁስ ነው፤

10/ **"Consignment"** means a specific amount of plant, plant product, or other regulated article that is transported, either separately or combined, all documented by a singule phytosanitary certificate;

፲፩/ **"የዕፅዋት ጥበቃ"** ማለት በሀገር ውስጥ የሚገኝ መደበኛ፣ የቅድመ ምርት፤ የድህረምርት፣ መጤ ወራሪና ተዛማች ተባይ በዕፅዋት እና ዕፅዋት ውጤት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የመከላከልና የመቆጣጠር አገልግሎት ነው፤

**11/ "Plant Protection"** means a service to prevent and control regular, pre-harvest, post-harvest, invasive, and migratory pests in the country from causing damage to plants and plant products;

፲፪/ **"ኳራንቲን"** ማለት ማንኛውም ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ወይም ጠቃሚ ዘአካልን ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ በተወሰነ ጊዜና ቦታ በማግለል ኢንስፔክሽን፣ ምርመራ፣ ምልከታ፣ ክትትል፣ ህክምና ወይም ምርምር ማድረግ ነው፤

12/ **"Quarantine"** means an officially designated procedure to confine a plant, plant product, regulated article, or beneficial organism at a specified place and time for inspection, testing, observation, follow-up, treatment, or research;

፲፫/ **“የዕፅዋት ኳራንቲን”** ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ እንዳይገባ ወይም እንዳይስፋፋ ኦፊሴላዊ ቁጥጥሩን ለማረጋገጥ የሚከናወን ማንኛውም ተግባር ነው፤

፲፬/ **“ተባይ”** ማለት ዕፅዋትንና የዕፅዋት ውጤት ጤናን የሚጎዳ ማንኛውም ዕፅዋት፣ እንስሳት እና በሽታ አምጪ ደቂቅ ዘአካል ነው፤

፲፭/ **“ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ”** ማለት ኳራንቲን ተባይን ወይም ኳራንቲን ተባይ ያልሆነ ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይን የሚያጠቃልል ነው፤

፲፮/ **“ኳራንቲን ተባይ”** ማለት በአንድ ሀገር ወይም አካባቢ ላይ ኤኮኖሚያዊ ተፅዕኖ የማድረስ እምቅ ኃይል ያለው፣ ነገር ግን በሀገሩ ወይም በአካባቢው የሌለ፣ ወይም ኖሮም ስርጭቱ በተወሰነ ደረጃ ብቻ የተገደበና ኦፊሴላዊ ቁጥጥር እየተደረገበት ያለ ተባይ ነው፤

፲፯/ **“ኳራንቲን ተባይ ያልሆነ ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ”** ማለት ማናቸውም ተባይ ሆኖ በሚዘራ፣ በሚተከል ወይም በሚራባ ዘር ላይ ወይም ውስጥ በመገኘቱ ምክንያት የመራባት ተልዕኮ ላይ ተቀባይነት የሌለው ጉዳት ያስከትላል ተብሎ በዝርዝር የተለየ ተባይ ነው፤

፲፰/ **“መደበኛ ተባይ”** ማለት ከቦታ ቦታ በቀላሉ የማይዛመት፣ ነባርና ከተለያየ ሰብል ጋር ዘላቂ ስነ-ህይወታዊ ቁርኝት ያለው በዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤት ላይ ጉዳት የሚያደርስ በሀገር ውስጥ ያለ ተባይ ነው፤

13/ “**Plant Quarantine**” means any activity carried out to ensure the official control of a regulated pest in order to prevent its introduction or spread;

14/ **“Pest”** means any species, strain, or biotype of plant, animal, or pathogenic agent injurious to plants and plant products;

15/ **“Regulated Pest”** means quarantine pest and regulated non-quarantine pest;

16/ **“Quarantine Pest”** means a pest of potential economic importance to the area endangered thereby and not yet present there, or present but not widely distributed and is being officially controlled;

17/ **“Regulated Non-Quarantine Pest”** means any pest whose presence in plants for planting affects the intended use of those plants with an economically unacceptable impact and which is therefore regulated;

18/ **“Regular Pest”** means a pest that is known to be present in the country and has a permanent biological relationship with different crops but does not migrate from one place to another easily and causes damage to plants and plant products;

፲፱/ **"ተዛማች ተባይ"** ማለት ከሀገር ወደ ሀገር በመዛመት እና በሚደርስባቸው አካባቢዎች በከፍተኛ ፍጥነትና ቁጥር በመራባት በዕፅዋት እና ዕፅዋት ውጤት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ተባይ ሲሆን ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይን አይጨምርም፤

፳/ **"መጤ ወራሪ ተባይ"** ማለት ሀገር በቀል ያልሆነ ከተፈጥሮ ሥነ-ምህዳሩ ውጪ ሲገኝ በዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤት ላይ ጉዳት እና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያደርስ በፍጥነት መራባትና መስፋፋት የሚችል ተባይ ነው፤

፳፩/ **"ድህረ-ምርት ተባይ"** ማለት ሰብል ተመርቶ ከተሰበሰበ በኋላ በማከማቻ፣ በማሸጊያ፣ በገበያ እና በሌሎች የምግብ አቅርቦት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ተባይ ነው፤

፳፪/ "**ደቂቅ ዘአካል**" ማለት ፋይቶፕላዝማ፣ ወይም ስፓይሮፕላዝማ ወይም ሬክቴሽያ ወይም ፈንገስ ወይም ባክቴሪያ ወይም ኔማቶድ ወይም ቫይረስ ሆኖ በማይክሮስኮፕ የሚታይ ህዋስ ነው፤

፳፫/ **"ሥነ-ሕይወታዊ ተባይ መከላከያ"** ማለት ማንኛውም ህይወት ያለው የውስጥና የውጭ ጥገኛ ወይም አዳኝ ወይም ደቂቅ ዘአካል ሆኖ ራሱን የሚተካ ፍጡር ወይም ለተባይ መከላከያነት የሚያገለግል የተፈጥሮ ጠላት ወይም ተፎካካሪ ወይም ተፃራሪ የሆነ ነው፤

፳፬/ **"የተፈጥሮ ጠላት"** ማለት እፅዋት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልን ተባይ በተፈጥሮው በተለያየ መንገድ ሊያጠቃና እዝበት መጠኑን ሊቀንስ የሚችል ህይወት ያለው ነገር ነው፤

19/ **"Migratory Pest"** means a pest that migrates from country to country and causes damage to plants and plant products by multiplying in large numbers and at a high rate in the areas it reaches, but does not include a regulated pest;

20/ **"Invasive-Alien Pest"** means an exotic pest found outside its natural environment, which can multiply and spread rapidly causing damage and adverse effects on plants and plant products;

21/ **"Post-Harvest Pests"** means pests that damage crop yields after harvesting and can occur during marketing, packaging, storage, and other stages of the food supply chain.;

22/ **"Microorganism"** means phytoplasma, spiro plasma, rickettsia, fungus or bacteria or nematode or viruses that can only be seen by magnifying devices;

23/ **"Biological Pest Control"** means any living internal or external parasite or predator or microorganism which is a self-replicating creature or a natural enemy or competitor or antagonist that serves for pest control;

24/ **"Natural Enemy"** means a living organism that can naturally attack plant pests in different ways and reduce the pest population density that can cause damage to plants ;

፳፭/ **“የኳራንቲን ጣቢያ”** ማለት ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባና ወደ ውጭ በሚወጣ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር በሚደረግበት ቁስ ላይ ኢንስፔክሽን የሚካሄድበት፣ ህክምና ሲሰጥ ክትትልና አሰሳ የሚደረግበት፣ የይለቀቅ ፈቃድ የሚሰጥበት፤ ወደውጪ ለሚላክ የዕፅዋት የጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጥበት እና አስፈላጊ ሲሆን ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ እንዲወገድ ውሳኔ የሚሰጥበት ቦታ ነው፤

25/ **“Quarantine Station”** means a place where specified activities of phytosanitary matters including carrying inspection, conducting supervision treatment, providing certificates, and release authorization are accomplished on plants, plant products and other regulated articles, imported into or exported from the country;

፳፮/ **“የመግቢያ እና መዉጫ በር”** ማለት አውሮፕላን ማረፊያ፣ ፖስታ ቤት፣ የባህርና የየብስ ወደብ፣ ወይም ማንኛውም ጭነት ወይም ሰው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባበት ወይም ከሀገር እንዲወጣበት የተሰየመ ቦታ ነው፤

26/ **“Entry and Exit Point”** means an airport, post office, seaport, land border point, or any other location officially designated for the importation and exportation of consignments or the entrance and exit of a person;

፳፯/ **“ኦፊሴላዊ”** ማለት በህግ የተደገፈ አሰራር ሆኖ ሥልጣን ባለው ሰው የሚከናወን ይፋዊ ሥራ ነው፤

27/ **“Official”** means a legal working process performed by an authorized person;

፳፰/ **“ኦፊሴላዊ ቁጥጥር”** ማለት የኳራንቲን ተባዮችን ለማጥፋት ወይም ለመገደብ ወይም ኳራንቲን ተባይ ያልሆኑ ቁጥጥር የሚደረግበትን ተባይ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዓላማ ያለው ተግባራዊ የሚደረግ አስገዳጅ የፋይቶሳኒተሪ ደንብ እና መመሪያ ነው፤

28/ **“Official Control”** means the active enforcement of mandatory phytosanitary Regulations and Directive with the objective of eradication or containment of quarantine pests or the management of regulated non-quarantine pests;

፳፱/ **“ተባይ አሰሳ”** ማለት በአንድ አካባቢ፣ ምርት የሚመረትበት አካባቢ ወይም ቦታ ላይ የተባዮች መኖር፣ አለመኖር፣ የተባይ ግኝት ወሰን ወይም ባህሪን ለመወሰን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚካሄድ ኦፊሴላዊ አሰራር ነው፤

**29/ “Pest Survey”** means an official procedure conducted over a defined period to determine the presence, absence, extent of occurrence, or characteristics of a pest in an area, place of production, or production site;

፴/ “ተባይ ቅኝት” ማለት በአንድ አካባቢ ስለ ተባዮች መረጃ በአጠቃላይ ክትትል፣ ልዩ ክትትል ወይም ሁለቱንም በማጣመር የሚከናወን ኦፊሴላዊ ሂደት ነው፤

፴፩/ **“ተባይ ክስተት ክትትል”** ማለት ከተባይ ቁጥጥር በኋላ ሰብሉ ለምርት እስኪደርስ ድረስ የሚደረግ እና የፋይቶሰኒተሪ ሁኔታዎችን ለማረጋገጥ ወቅታዊና ተከታታይነት ያለው ኦፊሴላዊ ሂደት ነው፤

፴፪/ **“ተባይ መከላከል”** ማለት በሰው፣ እንስሳትና አካባቢ ላይ ጉዳት የማያስከትል ሥነ-ህይወታዊ፣ ኬሚካል እና የተሻሻለ የሰብል አያያዝ ዘዴን በመጠቀም የተባይን ቁጥር በዘላቂነት ለመቀነስና ጤናማ ሰብል ለማምረት የሚያስችል ስልት ነው፤

፴፫/ **“ተባይ ወረርሽኝ”** ማለት የተመቻቸ ከባቢያዊ ሁኔታ ሲኖር የአንድን አካባቢ ሥነ-ምህዳር የተላመደ ተባይ እዝበት መጠን ከተለመደው በላይ መጨመር ክስተት ወይም የተዛማች ተባይ በሰፊ አካባቢ እና በከፍተኛ **እዝበት** መጠን መከሰት ነው፤

፴፬/ **“እዝበት መጠን”** ማለት አንድ ወይም የተለያዩ የተባይ ዝርያዎች በአንድ ወቅትና በአንድ አካባቢ የሚኖራቸው ብዛት ነው፤

፴፭/ **“ተባይ ጉዳት”** ማለት ተባይ በዕፅዋትና ዕፅዋት ውጤት ላይ የሚያደርሰው የምርት ብክነት፣ የጥራት ጉድለት እና የገበያ ተቀባይነት ማጣት ነው፤

**30/ “Pest Surveillance”** means an official process whereby information on pests in an area is obtained through general surveillance, specific surveillance, or a combination of both;

31/ **“Pest Outbreak Monitoring”** means a regular and continuous official process carried out after pest control operation until crop harvest and to ensure phytosanitary conditions;

32/ **“Pest Control”** means a strategy that applies biological, chemical, and improved crop management methods that do not cause harm to humans, animals, and the environment to sustainably reduce pest population for the production of healthy crops;

33/ **“Pest Epidemic”** means the sudden occurrence of pest population beyond the normal density or coverage of large area and high density of migratory pests due to favorable environmental conditions;

34/ **“Population Density”** means the number of one or more pest species present in a given area at a given time;

35/ **“Pest Damage”** means loss of production, quality, and failure to comply with the market requirement due to the effects of pests on plant and plant products;

፴፮/ **"ምርመራ"** ማለት የተባይ መኖርን ለማረጋገጥ፣ የተባይን ዓይነት ለመለየት፣ እንዲሁም አስፈላጊ የዕፅዋት ኳራንቲን ሁኔታ መሟላቱን ለማረጋገጥ በዕፅዋት፣ በዕፅዋት ውጤትና ሌላ ቁጥጥር በሚደረግበት ቁስ ላይ የሚደረግ ኦፊሴላዊ የላቦራቶሪ ውስጥ ፍተሻ ነው፤

፴፯/ **"ኢንስፔክሽን"** ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ አለመኖር እና አስፈላጊ የዕፅዋት ኳራንቲን ሁኔታ መሟላትን ለማረጋገጥ በዕፅዋት፣ ዕፅዋት ውጤትና በሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ላይ በዓይን ዕይታ የሚደረግ ኦፊሴላዊ ሥራ ነው፤

፴፰/ **"ተባይ ሥጋት ትንተና"** ማለት ሥነ-ህይወታዊ ወይም ሌላ ሳይንሳዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃ ላይ በመመሥረት ማንኛውም ህይወት ያለው ነገር የተባይነት ባህሪይ ያለው ስለመሆኑ፣ ተባዩ ቁጥጥር ሊደረግበት የሚገባ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑና ስለሚደረገው የኳራንቲን ቁጥጥር ጥንካሬ ለመወሰን የሚካሄድ የአሠራር ሂደት ነው፤

፴፱/ **"የተበከለ"** ማለት በሽታ አምጪ ደቂቅ ዘአካል የተገኘበት ወይም በበሽታ አምጪ ደቂቅ ዘአካል ጥቃት የደረሰበት ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ነው፤

፵/ **"የተወረረ"** ማለት ተባይ የተገኘበት ወይም በተባይ የተጠቃ ዕፅዋት፣ የዕዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ነው፤

፵፩/ **"ህክምና"** ማለት ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን ቁጥጥር ከሚደረግበት ተባይ ማንጻት ነው፤

36/ **"Testing"** means an official laboratory examination of plants, plant products, or other regulated articles, other than visual, to determine if pests are present, identify pests, or determine compliance with specific phytosanitary requirements;

37/ **"Inspection"** means official visual examination of plants, plant products, or other regulated articles to determine if the pest is present or to determine compliance with quarantine requirements;

38/ **"Pest Risk Analysis"**means the process of evaluating biological or other scientific and economic evidence to determine whether a pest should be regulated or not and to decide on the strength of any quarantine measure to be taken upon it;

39/ **"Infected"** means a plant, plant product or other regulated article in which a pathogenic micro-organism is present or has been attacked by it;

40/ **"Infested"** means a plant, plant product or other regulated article in which a pest is found or injured by pest;

41/ **"Treatment"** means the disinfection or disinfestation of plants, plant products, and other regulated articles from regulated pests;

፵፪/ **“ማስወገድ”** ማለት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ማሟላት ያለበትን የዕፅዋት ኳራንቲን መስፈርት ያላሟላ ጭነትን ወደመጣበት አገር በመመለስ ወይም በማምከን የሚከናወን ተግባር ነው፤

፵፫/ **“የማስገቢያ ፈቃድ”** ማለት ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ ሰነዱ ላይ በተገለፀው ሁኔታ ጭነት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በህትመት ወይም በኤሌክትሮኒክስ የሚሰጥ የቅድመ መግባት ፈቃድ ነው፤

፵፬/ **“የይለቀቅ ፈቃድ”** ማለት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚወጣ ጭነት ቁጥጥር ከሚደረግበት ተባይ ነፃ ሆኖ ከጉምሩክ እንዲለቀቅ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የኅትመት ወይም የኤሌክትሮኒክስ ውጤት የሆነ ሰነድ ነው፤

፵፭/ **“የዕፅዋት ጤንነት”** ማለት ሣይንሳዊና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው ደረጃ እና አሠራር ተከትሎ ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ በዕፅዋት ወይም በዕፅዋት ውጤት ላይ እንዳይኖርና ጉዳት እንዳያስከትል በመከላከልና በመቆጣጠር የሚረጋገጥ የዕፅዋት የጤና ሁኔታ ነው፤

፵፮/ “ፋይቶሳኒተሪ” ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት የዕፅዋት ተባይ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ ወይም እንዳይስፋፋ የመከላከል ዓላማ ያለው ማንኛውም ሕጋዊ ወይም አፊሳላዊ አሠራር ነው፤

፵፯/ **“የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት”** ማለት ኦፊሴላዊ የሆነ የህትመት ወይም የዚሁ ተመሳሳይ የሆነ ኦፊሴላዊ የኤሌክትሮኒክስ ውጤት ሆኖ በዓለም ዓቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት ከፀደቀው ሞዴል የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጋር የተጣጣመ ሰነድ ነው፤

**42/ “Disposal”** means a process of getting rid or dispos or sending it back to the country of export of a consignment that does not fulfill the requirement of plant quarantine to import;

**43/ “Import Permit”** means an official pre-entry document whether print or electronic authorizing the importation of a consignment following specified quarantine requirements;

44/ **“Release Authorization”** means an official printed document or its electronic version issued that the authority issues to customs verifying that the consignment is free of regulated pest;

45/ **“Plant Health”** means the health status of plants ensured through the prevention and control of regulated pests to ensure their absence and to prevent damage to plants or plant products, in accordance with scientific and internationally accepted standards and procedures;

46/ **“Phytosanitary”** means any legal or official measure aimed at preventing the introduction or spread of a regulated plant pest into a country;

47/ **“Phytosanitary Certificate”** means an official paper document or its official electronic equivalent, consistent with the model certificates of the IPPC, attesting that a consignment meets Quarantine import requirements;

፵፰/ **"ድህረ መግባት ኳራንቲን"** ማለት ዕፅዋት ወይንም የዕፅዋት ውጤት ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ለመጣበት ዓላማ ከመሠራጨቱ በፊት ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቦታ በማሳደግ የሚተገበር የኳራንቲን አሰራር ነው፤

፵፱/ **"ከተባይ ነፃ አካባቢ"** ማለት በሳይንሳዊ መረጃ በተደገፈ አንድ የተለየ ተባይ የማይገኝበት የሀገር ጥምረት፣ ሀገር፣ የሀገር ክፍል የሆነ እና እንደአስፈላጊነቱ ይህ ሁኔታ በይፋ ተጠብቆ የሚቆይ ነው፤

፶/**"ከተባይ ነፃ የሆነ የማምረቻ ቦታ"** ማለት አንድ የተለየ ተባይ እንደማይገኝበት በሳይንሳዊ መረጃ የተረጋገጠ የአካባቢ ውስን ክፍል ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ለተወሰነ ጊዜ በይፋ ተጠብቆ የሚቆይ ነው፤

፶፩/ **"ከተባይ ነፃ የሆነ የማምረቻ ስፍራ"** ማለት በሳይንስ በተደገፈ መረጃ አንድ የተወሰነ ተባይ የማይገኝበት የማምረቻ ቦታ ውስን ክፍል ሲሆን አስፈላጊ ከሆነ ይህ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ በይፋ ተጠብቆ የሚቆይ ነው፤

፶፪/ **"ዝቅተኛ የተባይ ክስተት አካባቢ"** ማለት አንድ የተወሰነ ተባይ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝበት እና ውጤታማ ክትትል ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትም ሙሉ ሀገር፣ የአንድ ሀገር አካል፣ ወይም ሁሉም ወይም የበርካታ ሀገራት ክፍሎች፣ ሆኖ በባለስልጣናት ተለይቶ የሚታወቅ አካባቢ ነው፤

48/ **"Post Entry Quarantine"** means a quarantine procedure implemented by raising plants or plant products in a place designated for that activity prior to the distribution of plants or plant products for the purpose for which it originated;

49/ **"Pest Free Area"** means a group of countries, a country, or a part of a country where, based on scientific evidence, a specific pest known not present and this status is officially maintained, as appropriate;

50/ **"Pest Free Place of Production"** means a limited part of an area where a specific pest is scientifically known not present and this status is officially maintained, as appropriate;

51/ **"Pest Free Production Site"** means a limited part of place of production where a specific pest is scientifically known not present and this status is officially maintained, as appropriate;

52/ **"Area of Low Pest Prevalence"** means an area where a particular pest is present at low levels and is effectively monitored or controlled, whether it is throughout a country, a portion of a country, or all or parts of multiple countries as determined by the appropriate authorities;

፶፫/ **“የኳራንቲን አስቸኳይ ጊዜ እርምጃ”** ማለት በድንገት ወይም ባልተጠበቀ ሁኔታ የዕፅዋት ኳራንቲን ተባይ ክስተት ሲያጋጥም በመደበኛ የኳራንቲን አሰራር መከላከል ወይም መቆጣጠር በማይቻልበት ወቅት የተባዩን ወደ አዲስ አካባቢ መግባትን ወይም መስፋፋትን ለመከላከል ወይም ለመገደብ የሚያስችል ድርጊት ነው፤

፶፬/ **“ዓለም አቀፍ ስምምነት”** ማለት እ.አ.አ አቆጣጠር በ፩ሺ፱፻፶፩ የተፈረመው እና በተከታታይ የተሻሻለው ዓለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት ነው፤

፶፭/ **“የአርሶና/አርብቶ አደር የመስክ ትምህርት ቤት”** ማለት ጣራና ግድግዳ የሌለው በአርሶና አርብቶ አደር ፍቃደኝነት የተቋቋመ በግብርና ባለሙያ የሚደገፍ የግብርና ማነቆዎችን በራስ አቅም የሚመራመሩበት እና መፍትሄ የሚሰጡበት ኢ-መደበኛ የመስክ ትምህርት ቤት ነው፤

፶፮/ **“የሰለጠነ ተባይ አሳሽ”** ማለት ከማህበረሰቡ የተመረጠ ሰልጣኝ ሆኖ ስለተባይ አሰሳ ምንንት፣ ዘዴ እና ሪፖርት አደራረግ በሚኒስቴሩ በተዘጋጀው የስልጠና ሠነድ መሠረት የዕፅዋት ጥበቃ ባለሙያ ስልጠና የተሰጠው ሰው ነው፤

፶፯/ **“ኢንስፔክተር”** ማለት ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ላይ የዕፅዋት ጤንነትን አስመልክቶ በወጣ መስፈርትና የህግ ማዕቀፍ መሰረት የቁጥጥር ተግባር እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው፤

፶፰/ **“ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር”** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

53/ **“Emergency Quarantine Action”** means an action taken to prevent or limit the introduction or spread of a plant quarantine pest to a new area when it is not possible to prevent or control it through regular quarantine procedures in the event of a sudden or unexpected occurrence of the quarantine pest;

54/ **“International Convention”** means the International Convention on Plant Protection signed in 1951 and successively amended;

55/ **“Agricultural/Pastoralist Field School”** means a non-formal field school, established voluntarily by agriculturalists or pastoralists and supported by an agricultural expert, conducted without roofs or walls, where participants can independently investigate and develop solutions to agricultural problems;

56/ **"Trained Pest Surveyor"** means a person selected from the community and trained by a plant protection professional in pest survey techniques, methods, and reporting, in accordance with the training document prepared by the Ministry;

57/ **“Inspector”** means a person authorized to carry out inspection activities on plants, plant products, and other regulated articles in accordance with established plant health standards and the legal framework;

58/ **“Ministry or Minister”** means the Ministry of Agriculture or Minister, respectively;

፶፱/ **“ባለሥልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ነው፤

፷/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፤

፷፩/ **“ተቆጣጣሪ አካል”** ማለት አግባብነት ያለው ህጋዊ ስርዓትን ተከትሎ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥር ላይ የተሰማራ በህግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ተቋም ወይም ድርጅት ነው፤

፷፪/ **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፷፫/ ማንኛውም በወንድ ፆታ አገላለጽ የተመለከተው የሴት ፆታንም ይጨምራል፡፡

፫. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ፡-

፩/ በዕፅዋት፣ በዕፅዋት ምርትና ምርታማነት ላይ ጉዳት በሚያደርስ ተዛማች፣ መደበኛ፣ መጤ ወራሪ፣ የድህረ ምርት ተባይ እና ልዩ ትኩረት በሚሻ መደበኛ ተባይ ላይ በሚደረግ መከላከልና ቁጥጥር፤

፪/ ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይን አስመልክቶ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር በሚላክ፣ በትራንዚት በሚተላለፍ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር በሚደረግበት ቁስ ላይ የሚካሄድ የዕፅዋት ኳራንቲን ሥራዎች ላይ፤

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ በሀገር ውስጥ እንዳይስፋፋና እንዳይሰራጭ በሚሰሩ የዕፅዋት ኳራንቲን ሥራዎች ላይ፤ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**59/ “Authority”** means Ethiopian Agricultural Authority;

**60/ "Region"** means any Region established according to Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administration;

**61/ “Regulatory Body”** means any institution or organization authorized by law to exercise control over the import and export of articles in accordance with the relevant legal system;

**62/ “Person”** means a natural or juridical person;

**63/** Any expression in the masculine gender includes feminine.

**3. <u>Scope</u>**

The Proclamation shall be applicable throughout the country:

1/ On regular, invasive alien, post-harvest, and migratory pests and pests that require special attention, that cause damage to plant and production and productivity of cultivated plants;

2/ On Plant quarantine activities carried out concerning regulated pests on imported, exported plants, plant products or other controlled articles or in-transit; and

3/ Without prejudice to the provisions of Sub Article (2) of this Article shall be applicable in plant quarantine activities related to the prevention and spread of regulated pests in the country.

## ክፍል ሁለት

## ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ

፬. **ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት**

፩/ ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ በሳይንሳዊ ጥናት እና በስጋት ትንተና ውጤት መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ ቢገባ በዕጽዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆን አለበት፤

፪/ ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ቁጥጥር ከሚደረግበት ተባይ ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከላኪው እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ በልዩ ሁኔታ በላኪውና ተቀባይ ሀገር በተስማሙበት የሚሰጥ ማስገቢያ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፤

፫/ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ማንኛውም ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ከጉምሩክ ከመለቀቁ በፊት አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ የሚገልጽ የይለቀቅ ፍቃድ ከባለስልጣኑ ሊሰጥ ይገባል፤

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በገደብ እንዲገባ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ዝርዝር ውስጥ የተካተተውን ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር በሚደረግበት ቁስ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የማስገቢያ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፤

## PART TWO

## IMPORTING AND EXPORTING PLANTS, PLANT PRODUCTS AND OTHER REGULATED MATTER

4. **Import**

1/ Any Importing plant, plant product, and other regulated matter shall be supported with scientific study and pest risk analysis as appropriate ensuring the import's are free from regulated pests that damage plant health and the environment.

2/ Any Importing plant, plant product, or other regulated article imported into the country shall have an import permit certifying that it is free from regulated pests and, in cases agreed upon by the exporting and importing countries, the regulated article shall the agreed Import permit;

3/ Any plant plant product or other regulated article shall have a release authorization issued by the authority before it is released from customs.

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, plants, plant products and other regulated matter covered in the determinate list prepared by the authority shall have an import permit.

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ ለመግባት በሌላ ሀገር በመተላለፍ ላይ የነበረን ሸቀጥ እሽጉ ተከፍቶ እንደገና የታሸገ እንደሆነ የመልሶ መላኪያ የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፤

፮/ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ከመፈቀዱ በፊት እንደ አስፈላጊነቱ የተባይ ቅኝት እና አሰሳ በማካሄድ ከተባይ ነፃ የሆነ የማምረቻ አካባቢ፣ ቦታ እና ስፍራ እንዲሁም ዝቅተኛ የተባይ ክስተት ያለበትን ሁኔታ በላኪው ሀገር የተለየ መሆኑን ማረጋገጫ መቅረብ ይኖርበታል፤

፯/ ማንኛውም ከውጭ ሀገር የሚገባ የእንጨት ማሸግያ በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ሕክምና የተደረገለት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና ምልክት ሊኖረው ይገባል፤

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አፈርን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ ማንኛውም ሰው አፈሩን ከማስገባት ጋር የተያያዘውን ሥጋት በማጠን፣ በጨረር፣ በሙቀት፣ በሙቅ አየር ጎጂ ህዋሳትን የማስወገድ ህክምና መቀነሻ እርምጃ መተግበር የሚችል መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፤

፱/ ማንኛውም በላኪው ሀገር የሚወሰደው አማራጭ የዕፅዋት ኳራንቲን ሕክምና ከዓላማው አንፃር የሚያስከትለው ውጤት ተመጣጣኝ ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

5/ Without prejudice to the provisions of this Article Sub Articles (1) and (2), consignment destined into the country but transiting through another country shall be accompanied with a re export phytosanitary certificate if the consignment is unpacked and repacked in the country of transit;

6/ Before authorizing import of plant, plant product or other regulated matter, as deemed necessary may need to confirm by exporter pest free area, pest free production place site and area of low pest prevalence through survey;

7/ Any wood packaging imported shall bear the logo and evidence which confirms that the treatment has been applied as per the International Convention;

8/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, any person importing soil into the country shall ensure that the risk reduction measures associated with the import of the soil are capable of being implemented through sterilization, irradiation, heat, or hot air treatment to eliminate harmful organisms;

9/ Any treatment applied on a consignment by the exporter shall be acceptable in the country if the treatment yields equivalent result to the prescribed treatment;

፲/ማንኛውም ልውጥ ህያው በደህንነት ህይወት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፭/፪ሺ፩ እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው የደንነት ህይወት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፮/፪ሺ፯ የተደነገጉትን አሟልቶ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ሚኒስቴሩ በተባይ ሥጋት ትንተና ውጤት መሠረት በዕፅዋት ጤና ላይ ጉዳት ማድረስ እንደማይችል ሲያረጋግጥ ነው፤

፲፩/ ሥነ-ህይወታዊ የተባይ መከላከያ አስፈላጊው የስጋት ትንተና ተደርጎለት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ፣ እንዲራባ፣ ተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል።

፭. <u>ድህረ መግባት ኳራንቲን</u>

፩/ ከውጭ የሚገባ ዕፅዋት ወይንም የዕፅዋት ውጤት አስፈላጊ የምርመራ ሥራ በሚሰራበት መልኩ የተደረጀና በተገለለ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ በግሪንሃውስ፣ በመስተዋት ቤት፣ በስክሪን ቤት፣ በፕላስቲክ ቤት ወይም በተገለለ ሥፍራ ለዚህ ተግባር እንዲያገለግል የወጣውን ዓለም-አቀፍ ስታንዳርድ የሚያሟላ መሆኑን በባለሥልጣኑ በተረጋገጠ መስክ ላይ በማሳደግና ክትትል በማድረግ ውጤቱን ተመርኩዞ መለቀቅ ወይም መከልከል አለበት፣

፪/ የዕፅዋት ጤንነት ስጋት ሆኖ የተለየ ወይም የሚለይ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት ወይም የዕፅዋት ውጤት የይለቀቅ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት በድህረ መግባት ኳራንቲን ማለፉ መረጋገጥ አለበት፣

10/ Any imported genetically modified organism shall comply with the provisions of the Biosafety Proclamation No. 655/2009 and the Biosafety (Amendment) Proclamation No. 896/2015, and may be imported into the country only when the Ministry certifies, based on the results of a pest risk analysis, that it will not cause harm to plant health;

11/ Following proper pest risk analysis, shall permit the importation, in-country production, use, and implementation of biological pest control.

**5. <u>Post Entry Quarantine</u>**

1/ Imported plants or plant products shall be grown and monitored by the Authority in a designated and isolated area for a specified period of time, in a greenhouse, glasshouse, screen house, plastic house, or other isolated facility, or in a field certified by the Authority as meeting international standards for this purpose, and shall be released or prohibited based on the results;

2/ Any plant or plant product imported from abroad that is considered a plant health risk must undergo post-entry quarantine before a permit for its release is granted;

፫/ በዕፅዋት ጤንነት ላይ ስጋት ይፈጥራል ተብሎ የሚለይ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤት ዝርዝር ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ም/ቤት በሚወጣ ደንብ ወይም በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ በተገለፀው መልኩ እንዲያድግ የተደረገው ዕፅዋት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ዕፅዋቱ ቁጥጥር ከሚደረግበት ተባይ ነጻ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

፮. **ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ**

፩/ ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ጭነት እንደ አስፈላጊነቱ ቁጥጥር ከሚደረግበት ተባይ ነጻ መሆኑ ወይም የተባይ ቅኝት እና አሰሳ በማካሄድ ዝቅተኛ የተባይ ክስተት ካለበት ወይም ከተባይ ነፃ የሆነ የማምረቻ አካባቢ፣ ቦታ ወይም ስፍራ የተመረተ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

፪/ ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ የተቀባይ ሀገር መስፈርት የማያሟላ ሆኖ ከተገኘ ወደ ተጠቀሰው ሀገር እንዳይላክ ይደረጋል፤

፫/ ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ጭነት ተቀባዩ ሀገር ከጠየቀ የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና እንደ አግባቡ መልሶ መላኪያ የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፤

፬/ ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ጭነት ከሀገር ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊውን የተቀባይ ሀገር መስፈርት ማሟላቱን የሚገልጽ የይለቀቅ ፍቃድ ሊኖረው ይገባል፤

፭/ ሥነ-ህይወታዊ የተባይ መከላከያን ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ ውጤታማነቱ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆን ይኖርበታል፤

3/ The list of plants and plant products to be identified as posing a risk to plant health shall be determined by a Regulation of the Council of Ministers or a Directive issued by the Ministry to implement this Proclamation;

4/ Plants grown in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be subject to appropriate monitoring to ensure that they are free from regulated pests.

6. **Export**

1/ Any plant, plant product or other regulated Article destined for export as may be appropriate shall through survey ensure a pest-free area, pest-free production place, site, and area of low pest prevalence;

2/ Plant, plant products or other regulated article that does not meet the requirements of the importing country, shall not be allowed for export to the said country;

3/ Any plant, plant product, or other regulated article destined for export shall be accompanied by a Phytosanitary Certificate and if appropriate with a Re-export certificate upon request by the importing country;

4/ Any consignment destined for export shall fulfill the requirements of the importing country before it leaves the country;

5/ Biological pest control agent is authorized for export if research has demonstrated its efficacy and safety;

፮/ ማንኛውም ከሀገር ውጭ የሚወጣ የእንጨት ማሸጊያ በዓለም አቀፍ ስምምነት መስፈርት መሰረት ሕክምና የተደረገለት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና ምልክት ሊኖረው ይገባል።

## ፯. ስለ ሕክምና

፩/ በማስገቢያ ፈቃድ መሠረት ሕክምና የሚያስፈልገው ማንኛውም ጭነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው የተጠቀሰው ሕክምና ወይም ተመሳሳይ ውጤት የሚሰጥ ሕክምና መከናወኑ ሲረጋገጥ ነው፤

፪/ ለውጭ ሀገር ገበያ በሚቀርብ ሸቀጥ ላይ የሚከናወን ሕክምና በተቀባዩ ሀገር ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ወይም ኢንስፔክተሩ በሚያከናውነው ኢንስፔክሽንና ምርመራ ውጤት መሠረት ሕክምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሰጠው ሰው ህክምና እንዲሰጥ ይደረጋል፤

፫/ ቁጥጥር በሚደረግበት ተባይ የተወረረ ወይም የተበከለ በዕፅዋት የተሸፈነ እርሻን የይዞታው ባለቤት በባለስልጣኑ የታዘዘውን ሕክምና በሚፈለገው ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል፤

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የተደነገገውን በማይፈጽም ባለይዞታ ላይ ባለሥልጣኑ ወጪውን በመሸፈን ህክምናውን በራሱ እንዲከናወን አድርጎ ከባለይዞታው ተመላሽ እንዲሆንና እንዲተካ ያደርጋል፤

6/ Any wood packaging destined for export shall bear the logo which confirms that the treatment has been applied as per the IPPC standards or its equivalent.

## 7. Treatment

1/ Any shipment requiring treatment under an import permit shall be imported into the country upon confirmation that the specified treatment or treatment with equivalent effect has been carried out;

2/ Treatment of any consignment destined for export shall be performed by a holder of a certificate of competence issued by the Authority, where such treatment is required by the requirements of the importing country or based on the findings of an inspection and examination conducted by an inspector;

3/ Any farm covered by plant infected or infested with a regulated pest shall be treated by the landholder with the prescribed treatment at the required time;

4/ In the case of an occupier who fails to comply with the provisions of Sub-Article (3) of this Article, the Authority shall cover the costs and arrange for the treatment to be carried out, and shall recover the costs from the occupier;

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የተወረረው ወይም የተበከለው በዕፅዋት የተሸፈነ እርሻ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ ወይም አርብቶ አደር ከሆነ ህክምናው የሚጠይቀው ወጪ እና ሥራ በመንግስት የሚሸፈን ይሆናል፤

፮/ ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ አደጋን የሚያስከትል ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያላቸው የፋይቶሳኒታሪ እርምጃዎችን በመጠቀም ተባዩን ለመከላከል እና ለማጥፋት አስፈላጊ ግብዓቶችን ለማሰባሰብ ለመንግስት ጥያቄ ያቀርባል።

፰. <u>ስለማስወገድ</u>

፩/ ተፈላጊውን የማስገቢያ መስፈርት ያላሟላ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ጭነት ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር እንዲወገድ ይደረጋል፤

፪/ በዓለም አቀፍ መጓጓዣ ላይ የሚጠራቀም የምግብ ትርፍራፊ ወይም ቆሻሻ ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ ሊሸከም ስለሚችል ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በአግባቡ እንዲወገድ ያደርጋል፣ ወጪውም በማጓጓዣው ባለቤት የሚሸፈን ይሆናል።

፱. <u>ስለማጥፋትና ስለመገደብ</u>

ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱ ከተረጋገጠ ተባዩ በኦፊሴላዊ ቁጥጥር ስርዓት በገባበት አካባቢ በተወሰነ ቦታ ተገድቦ እንዲቆይ ተደርጎ እንዲጠፋ ይደረጋል፡፡

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) of this Article, if the invaded or contaminated farm is a smallholder farmer or pastoralist bsad on the relevant law, the costs and work required by the treatment shall be cover by the Government;

6/ When it is confirmed that a regulated pest posing a significant national threat has entered the country, the Authority shall request the Government to mobilize the necessary resources to prevent and eradicate the pest using approved phytosanitary measures.

**8. <u>Disposal</u>**

1/ Any imported consignment that does not meet the entry requirements shall be disposed in collaboration with the relevant organ;

2/ Garbaged food left over from international transportation shall be disposed of by the Authority together with other relevant bodies as it can carry pests and diseases. The cost of disposal shall be borne by the transporter.

**9. <u>Containment and Eradication</u>**

In the event that entry of regulated pest is verified, the pest will be contained within a designated area and eliminated by an official control system.

## ክፍል ሦስት

## የተዛማች፣ መደበኛ እና መጤ ወራሪ ተባይ አሰሳ፣ ቅኝት፣ ክትትል፣ መከላከልና ቁጥጥር ስለማድረግ

### ፲. አሰሳ ስለማካሔድ

፩/ ተባይ በዕፅዋትና ዕፅዋት ውጤቶች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ፣ የቅድመ መከላከል ዝግጅት ለማድረግ ወቅትን መሠረት አድርጎ የተባይ ክስተት፣ እዝበት መጠንና የተወረረ ቦታን ለማወቅ አሰሳ ይካሄዳል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አሰሳው በማህበረሰቡ፣ በሰለጠነ ተባይ አሳሽና በግብርና ባለሙያ ሊካሄድ ይችላል፤

፫/ በመሬትና በአየር በተካሄደ አሰሳ የሚገኝ መረጃ በማጠናቀር ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

### ፲፩. የተዛማች ተባይ ቅኝት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፲) መሰረት ከተገኘ የአሰሳ ሪፖርት በመነሳት የክስተት ማረጋገጫ ቅኝት በባለሙያ ይካሄዳል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተገኘ መረጃን በመተንተን ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመከላከልና ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን የሚረዳ ቅድመ ሁኔታ መመቻቸት አለበት።

## PART THREE

## Surveillance, Survey, Monotoring, Prevention and Control of Regular, Migratory, and Invasive Allien Pests

### 10. Conducting Surviellance

1/ In order to prevent pest damage to plant and plant product, seasonal surveillance shall be conducted for the verification of pest occurance, pest population, and identification of infestated area;

2/ In accordance with Sub Acticle (1) of this Article, the surveillance may be conducted by the community in the assistance of trained surveyors and agricultural professionals;

3/ Information obtained from the ground and aereal surveillance shall be compiled for utilization.

### 11. Surveying Migratory Pest

1/ Based on the surveillance report obtained from the activity under Artcle (10) above, verification survey of pest occurance should be conducted by qualified officers;

2/ The information obtained from activity under this Article Sub Article (1) shall be analysed and used for pest forcasting, early warning and preparation of pest prevention and control action.

፲፪. **የመደበኛ ተባይ ቅኝት**

የመደበኛ ተባይ ቅኝት ኃላፊነት የአርሶና አርብቶ አደሩ እንዲሁም የሰፋፊ እርሻ ባለቤት ሆኖ ሚኒስቴሩ፡-

፩/ ተለይቶ በሚታወቅ ሰብል ተባይ ላይ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርስ ተባይ በሰብሉ ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት በቦታና በጊዜ ቅኝት በማከናወን ለመከላከልና ቁጥጥር ሥራ ለመስራት የባለሙያ እገዛ ያደርጋል፤

፪/ የተባይ ናሙና ተሰብስቦ በላቦራቶሪ ምርመራ ተደርጎ ምንነቱንና ዘሩ ተለይቶ አስፈላጊ መረጃ ተጠናቅሮ የላቦራቶሪ ውጤት ሰነድ፣ የመከላከልና ቁጥጥር ምክረ ሀሳብ ይሰጣል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር በተለየው ተባይ ላይ ተከታታይና ወቅታዊ የሆነ የተባይ ክስተት ስርጭት እና እዝበት መጠን መረጃ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ለተጠቃሚው ያሰራጫል።

፲፫. **የመጤ ወራሪ ተባይ ቅኝት**

ሚኒስቴሩ በሀገር ውስጥ የተስፋፉ መጤ ወራሪ ተባይ ላይ ወቅታዊ ቅኝት አድርጎ በብዝሀ ህይወት በግጦሽና በደን፤ በእርሻ ማሳ ውስጥና ድንበር፣ በውሃ አካል እና በመሳሰሉት ላይ መስፋፋትን መግታት የሚያስችል በቅንጅት የሚያሰራ ሥርዓት ይዘረጋል።

፲፬. **የተዛማች ተባይ ክትትል፣ መከላከል እና ቁጥጥር**

፩/ የተዛማች ተባይ ክትትል መከላከል እና ቁጥጥር ሥራ በሚኒስቴሩ አስተባባሪነት ከክልሎች ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

12. **Surveying Regular Pest**

The responsibility of survey of regular pest is vested on the grower while the Ministry:

1/ Provides professional assistance to the farmers to carry out pest control activities by carrying out a spatial and temporal survey of the pest that is identified and causes economic damage to the crop;

2/ Based on diagnosis of the sumitted pest specimen, identification shall be done to compile information that helps delivery of professional assisnace for perevention and control of pest;

3/ Based on the data of pest identified under Sub Article (2) of this Article, shall compile and analyze the subsequent and seasonal occurrence, distribution and population density of pest information and distribute to the user.

13. **Surveying Invasive Allien Pest**

To stop invasive pests from spreading into biodiversity, pastures, forests, agricultural areas, across borders, and into water bodies, the Ministry must set up a coordinated system to perform regular surveys on these pests.

14. **Migratory Pest Monitoring, Prevention and Control**

1/ In cooperation with the Regions, the Ministry shall coordinate migratory pest monitoring, prevention, and control efforts;

፪/ የተዛማች ተባይ ክስተት መጠን ሽፋንና አካበቢን መሰረት በማድረግ ለቁጥጥር የሚውል ግብዓት፣ ርጭት፣ ክትትል፣ ውጤታማነት እና የአካባቢ ተፅዕኖ ክትትልና ግምገማ ይደረጋል።

## ፲፭. የመደበኛ ተባይ ክትትል፣ መከላከል እና ቁጥጥር

በመንግስት የሚደረገው ሙያዊ ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ተባይ በወረርሽኝ ደረጃ እስካልተከሰተ ድረስ የአርሶና አርብቶ አደሩ ወይም የሰፋፊ እርሻ ባለቤቶች ኃላፊነቶች፡-

፩/ በወጥነት ኢኮኖሚያዊ ተባይ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፤

፪/ በሰብል ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልን ተባይ በተለያየ መንገድ የሚያጠቃና የተባዩን እዝበተ መጠን መቀነስ የሚችል የተፈጥሮ ጠላትን የመንከባከብና ጥቅም ላይ የማዋል ሥራ ይሰራል፤

፫/ የሰብሉን አስተዳደግ የሚያመቻቹ የተለያዩ የሰብል እንክብካቤ ዘዴን እንደ ባህላዊ የተባይ መከላከያ ዘዴን በመጠቀም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርስ ተባይ እዝበተ መጠን የመቀነስ ሥራ ይሰራል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተደረገን የመከላከል ሥራ አልፎ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርስ ተባይ እዝበተ መጠን ሲጨምርና ከአቅም በላይ ሲሆን ፀረተባይን በመጠቀም ቁጥጥር ይደረጋል፤

2/ Based on the occurrence of migratory pest and area coverage, shall carry out monitoring and assessment of resources required, followup, effectiveness and environmental impact.

## 15. Regular Pest Monitoring, Prevention and Control

Without prejudice to the professional support provided by the government, the responsibilities of farmers and pastoralists or large-scale farm owners, as long as the regular pest does not occur at an epidemic level, are:

1/ Prepare for the prevention and control of economic pests consistently;

2/ Encouragment of build up and utilization activities of the natural enemy that helps depree pest population level so as to minimize damages to crops;

3/ Implementation of different crop production practice that facilitate crop growth, such as traditional pest control method which result in reduction of pest population of economic impact may be performed;

4/ When the pest population increases to cause economic damage beyond the capability of prevention and control activities mentioned under Sub-Article (2) and (3) of this Article occurs, the pest shall be controlled using pesticides;

፭/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተዘረዘረው ቢኖርም የመደበኛ ተባይ መራባት እዝበተ መጠን ጨምሮ በወረርሽኝ ደረጃ ሲከሰት በሚኒስቴሩና በክልሎች ትብብር በቅንጅት የክትትል፣ መከላከል እና ቁጥጥር ሥራ ይከናወናል።

## ፲፮. መጤ ወራሪ ተባይ ክትትል፣ መከላከል እና ቁጥጥር

፩/ ሚኒስቴሩ የተስፋፋ መጤ ወራሪ ተባይ ዕፅዋት አመራረት ላይ ያለውን የተጽዕኖ ልክና ደረጃ ተከታታይነት ያለው ግምገማ ያካሂዳል፤

፪/ የተስፋፋ መጤ ወራሪ ተባይ ተጽዕኖን ለመግታትና ለመቀነስ ማህበረሰብ ተኮር የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር መካሄድ አለበት፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የተስፋፋ መጤ ወራሪ ዕፅዋት ጥቅም ላይ በማዋል መቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።

## ፲፯. የተቀናጀ የተባይ ክትትል፣ መከላከል፣ ቁጥጥር እና የዕፅዋት እንክብካቤ

፩/ አርሶና አርብቶ አደሩ ወይም የሰፋፊ እርሻ ባለቤት ጤንነቱ የተጠበቀ ዕፅዋት ለማምረት እና የአካባቢ ተጽዕኖን የሚቀንስ የተቀናጀ የተባይ ቁጥጥርና የዕፅዋት እንክብካቤ ሥራ ይሠራል፤

፪/ ውጤታማ የሆነ የተቀናጀ የተባይ ቁጥጥርና የዕፅዋት እንክብካቤ ሥርዓት ለመተግበር እና ለማስፋፋት ሊረዳ የሚችል የአርሶና አርብቶ አደር የመስክ ትምህርት ቤት እንዲቋቋምና እንዲሰፋፋ ይደረጋል፤

5/ When the pest population reaches an outbreak level, preventative and control measures must be carried out in coordination and cooperation between the Ministry and the Regions, regardless of the provisions of Sub-Articles (1) to (4) of this Article.

## 16. Invasive Allien Pest Monitoring, Prevention and Control

1/ The Minister may conduct a subsequent assessment of the extent and level of the impacts of widespread invasive pests;

2/ Community-based prevention and control measures shall be implemented to prevent and reduce the impact of widespread invasive pests;

3/ Subject to what is mentioned in Sub Article (2) of this Article, management by utilization system may be developed to control the widespread invasive plant.

## 17. Integrated Pest Monitoring, Prevention, Control, and Crop Care

1/ Farmers, pastoralists, or large-scale farm owners shall implement integrated pest management and plant care practices to ensure the production of healthy plants and to minimize adverse impacts on the environment;

2/ For the implementation and expansion of fruitful integrated pest control and crop management system, farmers field school will be established and expanded;

፫/ አርሶና አርብቶ አደሩ የተባይ ልየታና ቁጥጥር መረጃና ምክረሀሳብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

**፲፰. የድህረ-ምርት ተባይ መከላከልና መቆጣጠር**

፩/ በተባይ የሚደርስ የድህረ-ምርት ጉዳትና ብክለት ሊቀንስ የሚችል የምርት አሰባሰብ፣ አከመቻቸት፣ አያያዝና አጠቃቀም፣ እውቀትና ዘዴ ማስፋፋትና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፤

፪/ ቁጥጥርን ማጠናከር የሚያስችል ቴክኖሎጂ በሀገር ውስጥ በስፋት እንዲመረትና ከውጪ አገር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ለተጠቃሚ እንዲደርስና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤

፫/ የድህረ-ምርት ተባይ መከላከልና መቆጣጠር ቴክኖሎጂ እና የአሠራር ዘዴ በጥቅም ላይ እንዲውል የሚደረገው በአመዛኙ በሰውና በእንስሳ ጤናና በአካባቢ ላይ ጉዳትና ብክለት የማያደርስ ከሆነ ብቻ ነው።

## ክፍል አራት
## የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

**፲፱. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት**

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡-

፩/ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎትን ውጤታማነት የሚያጎለብት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ የአሠራር ሥርዓትን፣ የአተገባበር ዘዴን ይቀርጻል፤ ሲጸድቅም በበላይነት ተፈጻሚነታቸውን ይመራል፣ ያስተባብራል፤

3/ Farmers and pastoralists will be adviced for the utilization of information on pest identification and control.

**18/ Post Harvest Pest Prevention and Control**

1/ Promote and ensure the implementation of knowledge and methods for the collection, processing, handling, and use of produce in ways that reduce post-harvest damage and loss caused by pests;

2/ Ensure that technology capable of strengthening pest control is produced domestically and imported as necessary, so that it is made available to users and effectively implemented;

3/ Postharvest prevention and control operation system and technology generally should only be implemented if it does not have damage and loss on human and animal health and environment.

## PART FOUR
## POWER AND DUTY OF THE MINISTRY, AUTHORITY, AND THE INSPECTOR

**19. Power and Duty of the Ministry**

The Ministry shall have the following powers and duties:

1/ Taking the existing conditions into account, design policy, strategy, procedure, and method of implementation that enhance the effectiveness of plant protection services; and when approved, oversees and coordinate their implementation;

፪/ ሀገር በቀል የዕፅዋት ጥበቃ ቴክኖሎጂ ወደ ምርት በመለወጥ ለሚሳተፍ አካል ሚኒሰቴሩ ጠቀሜታቸውን፣ ውጤታማነታቸውን እና አዋጪነታቸውን በማረጋገጥ እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍ ያደርጋል፤

፫/ የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት በተመለከተ የሚያጋጥም ተግዳሮትን በምርምር እንዲፈታ በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በመነጋገር በምርምር የሥራ ዕቅድ እንዲካተት ይደረጋል፤

፬/ ዕፅዋት ጥበቃ ለሚያጋጥመው ተግዳሮት ትኩረት በመስጠት በምርምር መረጃ፣ ዕውቀት፣ ቴክኖሎጂ ወይም የአሰራር ስርዓት እንዲፈልቅ፣ እንዲላመድ፣ እንዲሻሻል ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ድጋፍ ይሰጣል፤

፭/ የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎትን ውጤታማነት የሚያጎለብት ለተዛማች፣ ለመደበኛ እና ለመጤ ወራሪ እና ድህረ ምርት ተባይ ቁጥጥርን በተመለከተ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ የአቅም ግንባታ ሥራን ይሰራል፤

፮/ በመደበኛ ተባይ ላይ ወቅታዊ አሰሳና ቅኝት በማድረግ እንዲሁም ከበርካታ ምንጮች መረጃን በማሰባሰብ የተባይ ዝርዝርን አዘጋጅቶ መረጃውን ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ ያደርጋል፤

፯/ የመደበኛ፣ የተዛማች እና መጤ ወራሪ ተባይ አሰሳ፣ ቅኝት፣ ክትትል፣ የመከላከልና ቁጥጥር ቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣ በበላይነትም ይመራል፤ ያስተባብራል፤

2/ Provide support, as necessary, to entities involved in the conversion of indigenous plant protection technologies into production by verifying their usefulness, effectiveness, and feasibility;

3/ Discuss with the legally authorized body to address the challenges of plant protection services through research and shall be incorporated into a research work plan;

4/ Recognize the challenges the Plant Protection Service has and assist it by establishing favorable circumstances for the development, modification, and enhancement of research data, expertise, technology, or technique;

5/ Develops and implements an operational system to improve the plant protection pest management service concerning regular, migratory, post-harvest, and invasive pests; conducts capacity building activities;

6/ Conduct regular pest surveys and surveillance, and compile a pest list by collecting information from multiple sources and making the information available to the relevant authorities;

7/ Lead, coordinate, and provide technical assistance for surveillance, surveying, monitoring, prevention, and control of regular, invasive alien species, migratory and post-harvest pests;

፰/ የተቀናጀ የተባይ ክትትል፣ መከላከል፣ ቁጥጥር እና የሰብል እንክብካቤ ሥርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፱/ የድህረ-ምርት ተባይ መከላከልና መቆጣጠር ግንዛቤ የመፍጠርና ተግባራዊ የማድረግ ሥራን ያስተባብራል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤ ይመራል፤

፲/ የዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎትን ውጤታማነት ለማጎልበት አስፈላጊ የሆነውን ሀብት የማልማት፣ የማፈላለግ፣ የማሟላት ሥራን በኃላፊነት ያከናውናል፤

፲፩/ የተዛማች ወይም መደበኛ ተባይ ክስተት በወረርሽኝ ደረጃ ከፍተኛ ሀገራዊ ስጋት ከፈጠረ ወረርሽኙን ለመግታት የሚያስችል አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ ለመንግስት ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ በማሰጠት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፲፪/ በዓለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነትና በሀገሪቱ ፖሊሲ መሠረት ባለሥልጣኑ ተወካይ ሆኖ ግዴታና ኃላፊነትን በሚጠበቀው ደረጃ መወጣት እንዲችል ሁኔታዎችን ያመቻቻል ይደግፋል።

፳. **<u>የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ ባለስልጣኑ በሀገሪቱ ሕግና ደንብ በተደነገገው መሠረት የዓለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት ግዴታና ሀላፊነት ለመወጣት ይሰራል፤

8/ Establishes and implements an integrated pest monitoring, prevention, control, and crop care system;

9/ Leads, coordinates, and provides technical assistance for the awareness raising and implementation of post-harvest pest prevention and control activities;

10/ Responsibly carries out the work of resources mobilization and supplementing to enhance the efficiency and effectiveness of plant protection services;

11/ In the event that a migratory or regular pest infestation constitutes a high national threat at an epidemic level, it shall request the Government to authorize emergency measures to suppress the epidemic and oversee their execution upon approval;

12/ Facilitates and supports the conditions for the authority to fulfill its duties and responsibilities as a representative in accordance with the International Plant Protection Convention and national policy.

20. **<u>Power and Duty of the Authority</u>**

The Authority shall have the following powers and duties:

1/ The Authority shall discharge the obligations and responsibilities arising from the International Plant Protection Convention in accordance with the laws and Regulations of the country;

፪/ ከሚመለከተው የክልል አስተዳደር ጋር በመተባበር አግባብነት ባለው አካባቢ የኳራንቲን ጣቢያ ያቋቁማል፤ለሚመለከተው ተቋም ስለጣቢያው መቋቋም ያሳውቃል፤

፫/ የተባይ አሰሳ እና ቅኝት በማካሄድ የተባይ ክስተት ሁኔታን መረጃ ያደራጃል፣ በመረጃዉ መሰረት ቁጥጥር የሚደረገበት ተባይ ዝርዝር ያዘጋጃል፤ ለሚመለከተው አካል መረጃ ይሰጣል፣ ያሻሽላል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤

፬/ ከኢንስፔክተሩ በሚያገኘው መረጃ መሰረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጭነት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ ይከለክላል፣ በቁጥጥር ሥር ያውላል፣ ህክምና እንዲሰጠው ያዛል፣ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት ሀገር እንዲመለስ ያደርጋል፤

፭/ የኳራንቲን አስቸኳይ ጊዜ እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልገው ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ ችግር ሲከሰት በወቅቱ ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ይወስናል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፮/ የዕፅዋት ተባይ ልየታ፤ ምርመራ እና ድኅረ መግባት የዕፅዋት ኳራንቲን ሥራን ይሰራል፣ አግባብነት ላለው አካል ዕውቅና ወይም ውክልና ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሁለቱንም ይሰጣል፤

፯/ ቁጥጥር በሚደረግበት ተባይ የተበከለ ወይም የተወረረ ማንኛውም ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤትና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ላይ አስፈላጊውን የኳራንቲን እርምጃ ይወስዳል፤

፰/ ቁጥጥር በሚደረግበት ተባይ የተበከለ ዕፅዋት፣ ዕፅዋት ውጤትና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ ይከለክላል፤ ለላኪው ሀገር የማሳወቂያ መረጃ ይልካል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ መጣበት ሀገር ይመልሳል፤

2/ Establishes quarantine station at appropriate place in collaboration with regional administration and inform relevant institutions about such establishment;

3/ Organizes pest incident status information by conducting pest surveillance and surveys, prepares a regulated pest list based on the information, and provides the same to the relevant bodies; updates and put in use;

4/ Based on the information obtained from inspector, when necessary, prohibits entry, holds and prescribes treatment, dispose or return to the importing country;

5/ Decides the occurrence of emergency quarantine situation, the emergency action to be taken; follows up and ensures the implementation of such actions;

6/ Performs diagnosis of plant pests, carries out tests and conduct post entry quarantine activities; delegates or provides recognition or both as necessary, to appropriate body;

7/ Takes necessary action on infected or infested plants, plant products and other regulated articles by regulated pest;

8/ Prohibits entry of plants, plant product and other regulated article infected or infested with regulated pest, notifies the exporting country; returns to the country of origin when found necessary;

፱/ ለዕፅዋት ኳራንቲን ሥራ አስተዋፅኦ፣ ድጋፍ እና ክፍተት የሚሞላ ማንኛውም ምርምር የሚያስፈልግ ጉዳይን በመለየት በህግ ሥልጣን ከተሰጠው ማንኛውም አካል ጋር በትብብር ይሰራል፤

፲/ ለዕፅዋት ጥበቃ አገልግሎት የሚውል የምርምር ውጤት ለተጠቃሚ ከመተላለፉ በፊት የተቀባይነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፲፩/ ማንኛውንም ድርጅታዊ ወይም ተቋማዊ መዋቅር ወይም ሌላ የኳራንቲን ጉዳይ ላይ ለውጥ ሲደረግ ለዓለም አቀፍ ዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት ሴክሬታሪያት እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤

፲፪/ የዕፅዋት ኳራንቲን ኢንስፔክሽን ተግባር የሚያከናውን ኢንስፔክተር ይመድባል፤

፲፫/ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበትን ቁስ የጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፲፬/ የዕፅዋት ኳራንቲን አገልግሎት ተቋምና የባለሙያን አቅም ይገነባል፤ ተከታታይ እና ወቅታዊ የሆነ ስልጠና ይሰጣል፤

፲፭/ ሀገራዊ የኳራንቲን መረጃን ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና የኳራንቲን ተባይ ክስተት ሪፖርት ለማድርግ ከሚመለከተው አካል መረጃ ይጠይቃል፤ መረጃውን ያደራጃል፤

፲፮/ የተባይ ሥጋት ደረጃን መሠረት አድረጎ ጭነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባበትን የመግቢያ በር ይወስናል፤

9/ Identifying research requirements in plant quarantine services and collaborating with any legally permitted organization that fills in the gaps;

10/ Issues a certificate of acceptance for plant protection research result before it is accessible by the user;

11/ Reports any structural changes of organization or institution and other quarantine related issues to the secretariat of the International Plant Protection Convention and other concerned bodies;

12/ Assigns inspector who performs plant quarantine inspection;

13/ Issues phytosanitary certificate for exportable plant, plant product and other regulated articles;

14/ Builds institutional capacity including human capacity of the quarantine service; provides continuous training in a timely manner;

15/ It shall request information from the relevant body to collect, organize, and report national quarantine information and the occurrence of quarantine pests; it shall organize the information;

16/ Based on the level of pest risk, determines the entry point for a consignment;

፲፯/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ በተደነገገው እና በሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ፋይቶሳኒታሪ ደረጃዎች መሠረት አግባብነት ያለው የፋይቶሳኒታሪ እርምጃዎችን ወክሎ እንዲያከናውን ብቃት ላለው አካል ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፲፰/ ሥነ-ሕይወታዊ የተባይ መከላከያ እና ሌሎች ጠቃሚ ዘአካል ማስገባትን፣ ማራባትን፣ ወደ አካባቢ መልቀቅን እና ማጓጓዝን ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፱/ ሥነ-ህይወታዊ የተባይ መከላከያ አስፈላጊው የስጋት ትንተና ተደርጎለት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ፣ እንዲራባ፣ ተግባር ላይ እንዲውል እና ወደ ውጭ አገር እንዲላክ ይፈቅዳል፣ ቁጥጥር ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፳/ በሀገሪቱ ውስጥ ሰለተከሰተ አዲስ ተባይ መረጃው ያሰበስባል፣ ያደራጃል እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል።

## ፳፩. የኢንስፔክተሩ ተግባርና ኃላፊነት

ኢንስፔክተሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ ማንኛውንም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚወጣ ወይም በትራንዚት የሚተላለፍን ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ላይ አስፈላጊውን ኢንስፔክሽን ያከናውናል፤

፪/ ከጭነቱ ጋር የተያያዘ ሰነድን ይፈትሻል፣ ሲያስፈልግም ቅጂ ይወስዳል፤

17/ When necessary, the Authority may delegate to an authorized entity the power to implement appropriate phytosanitary measures on its behalf in accordance with the provisions of this Proclamation and relevant international phytosanitary standards;

18/ Authorizes and regulates the production transportation and release of biological pest control agents and other beneficial microorganisms to the environment;

19/ Biological control agents shall be allowed to be imported, reproduced, released to the target pest, and exported after completing the necessary risk analysis; their application will be monitored, regulated, and overseen;

20/ Gathers information, compiles it, and either takes action or orders action to be taken when a new pest appears in the nation.

## 21. Powers and Duties of the Inspector

The Inspector shall have the following powers and duties:

1/ Shall conduct the necessary inspections on any plant, plant product, or other regulated article entering, leaving, or in transit through the country;

2/ Examine quarantine documents and, where necessary, take copies of such documents;

፫/ ጭነቱን ቁጥጥር ከሚደረግበት ከተባይ ነፃ ስለመሆኑ ኢንስፔክት የማድረግ፣ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ለጊዜው በማገድ በምርመራ እንዲረጋገጥ ማድረግ፣ በሚገኘው ውጤት መሠረት እንዲለቀቅ ወይም እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት ሀገር እንዲመለስ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ያደርጋል፤

፬/ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበትን ቁስ ጤንነት ያረጋግጣል፤

፭/ አጭር የጊዜ ቆይታ ያለው አትክልትና ፍራፍሬ፣ ቲሹ ካልቸር ዕፅዋት፣ ችግኝ፣ የዕፅዋት ቁርጥራጭ፣ ሥነ ህይወታዊ ነገርን በተመለከተ ብልሽትንና ጥፋትን ለመቀነስ እንዲቻል ተፈላጊውን መስፈርት እስካሟላ ድረስ በቅድሚያ እንዲስተናገዱ ያደርጋል፤ ዝርዝር መስፈርቱ ወደፊት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚወጣ መመሪያ የሚገለጽ ይሆናል፤

፮/ በትጋት፣ በታማኝነት፣ በጥንቃቄ እና በተቻለ ፍጥነት ሥራውን ይፈፅማል፤ የበላይ ኃላፊን ትዕዛዝ በማክበር ይሰራል፡፡

## ፳፪. <u>የኢንስፔክተሩ ግዴታ</u>

ኢንስፔክተሩ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በዕፅዋት ጤንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትል ቁጥጥር የሚደረግበት ተባይ መኖሩን ሲጠራጠር ወይም መረጃ ሲደርሰው በማንኛውም ሰዓት፣ በማንኛውም ሥፍራ ወይም መጋዘን በመግባት እንዲሁም ማጓጓዣ በማስቆም ኢንስፔክሽን የማካሄድ፤

3/ Inspect consignments to verify the absence of regulated pest; where suspicion arises, temporarily suspend the consignment for further inspection and report to the Authority for release, disposal, or return to the country of origin based on the inspection results;

4/ Ensure the health status of plants, plant products, and other regulated articles intended for export;

5/ Vegetable and fruit, tissue culture plant, seedling, plant cutting, and other biological material with a short shelf life shall receive priority inspection, provided that they meet the prescribed requirements to minimize damage or deterioration. The detailed criteria shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry;

6/ Shall perform his duties diligently, honestly, carefully, and as expeditiously as possible, and shall act in accordance with the orders of his superior.

## 22. <u>Obligation of the inspector</u>

The inspector shall have the following obligations:

1/ To conduct inspection at any time and at any location or warehouse, and to stop transportation when the presence of a regulated pest harmful to plant health is suspected or upon receipt of relevant information;

፪/ ሥራውን ከማከናወኑ በፊት ማንነቱንና የመጣበትን መስሪያ ቤት፣ ለምን እንደመጣ፣ ጭነቱን ኢንስፔክት የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት በመግለጽ የባለስልጣኑን መታወቂያ የማሳየት፤

፫/ ለሚወሰነው ውሳኔ ኢንስፔክተሩ ጭነቱን በተመለከተ እንደአስፈለጊነቱ ናሙናን፣ መጠንን ወይም ልኬታን፣ የሰነድ ቅጂ፣ ፎቶግራፍን፣ የቪዲዮ እና ተቀባይነት ያላቸውን ሌሎች ማሰረጃዎች የመያዝ፣ የመሰብሰብ እና አግባብ ላለው አካል የማቅረብ፤

፬/ የዚህን ህግ ዓላማ ለማሳከት በሚያግዝ ሁኔታ፣ ህግ በሰጠው ወሰን ውስጥ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱን ህጎችና የሥነ-ምግባር ኮዶች ባከበረ እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የመተግበር፤

፭/ የአዋጁንና ሌሎች የማስፈጸሚያ ህጎች መጣስን ሲያውቅ እንደአግባቡ ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፤

፮/ በሥራው ምክንያት የሚያገኘውን ምስጢራዊ መረጃ ወይም ሰነድ በሚስጥር የመጠበቅ::

2/ Prior to conducting any inspection, the Inspector shall present the identification issued by the Authority, specifying the identity, office of origin, purpose of the visit, and the assigned responsibility for inspecting the consignment;

3/ For the purpose of making a decision, the Inspector may, as necessary, take or collect samples, quantities or measurements, copies of documents, photographs, videos, and other acceptable evidence regarding the consignment, and submit them to the appropriate authority;

4/ Shall enforce this law in a manner that advances its objectives, within the limits established by law, and in full respect of other applicable laws and codes of conduct of the country;

5/ Shall promptly report to the Authority any breach of this Proclamation or related implementing regulations, as appropriate;

6/ Shall keep confidential any information or documents obtained in the course of performing duties.

፳፫. **ቅጣት**

፩/ ማንኛውም ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ከውጪ አገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ ወይም ከሀገር ውስጥ ወደ ውጪ አገር የሚያስወጣ ወይም ኢንስፔክተሩ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር እንዳይፈጽም ሆን ብሎ በኃይል፣ በዛቻ ወይም በማንኛውም መንገድ የከለከለ፣ ማስረጃ ወይም ናሙና እንዳይወሰድ ያደረገ፤ ማስረጃ ያጠፋ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ፤ ምርመራ ለማደናቀፍ ሀሰተኛ ማስረጃ ወይም መረጃ በመስጠት ያሳሳተ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ ብር) ይቀጣል፤

፪/ የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚያስችለውን ፍሬ ነገር፣ መረጃ ወይም ማስረጃ ሆን ብሎ በተገቢው ጊዜ ሳያሳውቅ ወይም ሳይሰጥ በመቅረቱ በዕፅዋት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ ከሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል የእስራት ቅጣት ይቀጣል፤

፫/ ኢንስፔክተሩ ሆን ብሎ ሐሰተኛ ሪፖርት ካቀረበ፤ መፈጸም የሚገባውን ተግባር ሳይፈጽም የቀረ ወይም በተገቢው ሁኔታ እርምጃ ሳይወስድ የቀረ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤

፬/ ኢንስፔክተሩ የማስገቢያ ፍቃድ የሚጠይቁትን ዕፅዋት፤ የዕፅዋት ውጤትና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ቁሶች ፈቃድ ሳይኖራቸው የይለቀቅ ፍቃድ ሰጥቶ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፤

23. **Penality**

1/ Any person who imports a plant, plant product, or other regulated article from abroad, or exports to another country, and intentionally prevents an Inspector from exercising his or her authority or duties by force, threat, or any other means; prevents evidence or samples from being taken; destroys or causes evidence to be destroyed; or misleads the Inspector by providing false evidence or information to obstruct an investigation, shall be punished with imprisonment for a term of one to five years or a fine of up to Birr 100,000 (One Hundred Thousand Birr), as the case may be;

2/ Whoever intentionally fails to notify, or timely provide, facts, information, or evidence that would allow for corrective action, thereby causing damage to plants, shall be punished with imprisonment for a term of one to three years;

3/ If the Inspector intentionally submits a false report, fails to perform the required duties, or fails to take appropriate action, the Inspector shall be liable to imprisonment for a term of one to three years;

4/ If the Inspector permits the importation of plants, plant products, or other regulated articles requiring an import permit without such a permit, the Inspector shall be liable to imprisonment for a term of one to five years;

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተገለጸውን ድርጊት በቸልተኛነት የተፈጸመ ከሆነ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤

፮/ ባለስልጣኑ የኳራንቲን ቦታ ብሎ በከለለው መሬት ላይ መወሰድ ስለሚኖርበት እርምጃ የሚሰጠውን ትዕዛዝ የተላለፈ ሰው ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፳ ሺ. እስከ ብር ፴ ሺ. የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፬. መረጃ የመስጠት ግዴታ

ማንኛውም በሀገር ውስጥ ሰለተከሰተ አዲስ ተባይ ያወቀ ሰው ለባለሥልጣኑ መረጃ የመስጠትና የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

፩/ በሀገር ውስጥ ሰለተከሰተ አዲስ ተባይ ያወቀ ማንኛውም በዕፅዋት ልማትና ጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰራ፡- መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆነና የግል ድርጅት፣ ባለሙያ ለባለሥልጣኑ መረጃ የመስጠትና የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

፪/ የመግቢያ ፈቃድ ያልተሰጠው ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን ይዞ መግቢያና መውጫ በር የደረሰ ማንኛውም ሰው ለባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም በመግቢያና መውጪያ በር የተሰማራ ተቆጣጣሪ አካል በስራው ምክንያት ከውጭ አገር ወደ ሀገር ውስጥ ዕፅዋት፣ ዕፅዋት ውጤት እና ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ሲያጋጥመው እንዲገባ ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት ለባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

5/ If the act specified in Sub-Articles (3) and (4) of this Article is negligently committed, the offender shall be liable to imprisonment for a term of six months to one year;

6/ A person who disobeys an order issued by the Authority regarding measures to be taken on land designated as a quarantine area shall be liable to imprisonment for a term of one to two years or a fine of Birr 20,000 to 30,000.

## Part Five
## Miscellaneous Provisions

### 24. Obligation to Provide Information

Anyone who came to know a new pest occurance in the country shall notify the authorities and provide the information.

1/ Any person working in plant production and protection whether governmental, non-governmental, or private; a professional; who becomes aware of a new pest occurring in the country shall notify the Authority and provide relevant information.

2/ Any person who arrives at an entrance or exit gate with unauthorized plants, plant products, or other regulated articles shall report to the inspector of the Authority.

3/ Any regulatory body engaged in entry or exit control shall notify the inspector of the Authority before granting permission for the importation of plants, plant products, or other regulated articles from abroad if, in the course of its duties, it encounters such articles.

**፳፭. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

፩/ ዕፅዋትንና አዝርዕትን ለመጠበቅ የወጣው ድንጋጌ ቁጥር ፶፮/፩ሺ፱፻፷፫ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፮. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

የዕፅዋት ኳራንቲን ደንብ ቁጥር ፬/፩ሺ፱፻፹፬ ሌላ ደንብ እስኪወጣ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

**፳፯. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወጣ ደንብን ለማስፈጸም የሚያስፈልግ መመሪያን ሊያወጣ ይችላል።

**፳፰. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**25. <u>Repealed Laws</u>**

1/ A Decree to provide for Plant protection No. 56/1971 is hereby repealed.

2/ No law or customary practice shall be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation in so far as it is inconsistent with this Proclamation.

26. **<u>Transitional Provisions</u>**

The plant Quarantine Regulation No. 4/1992 shall remain enforced until the new Regulation pursuant to this Proclamation is issued.

27. **<u>Power to Issue Regulation and Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations to implement this Proclamation.

2/ The Ministry based on this Proclamation and on this Article Sub-Article (1) may issue Directive to implement this Regulation.

**28. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 7th day of May, 2026**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**